# የኛ ህልም ለወያኔ ቅዠት ፣ የኛ ገነት ለሱ ገሀነም
# እኛና ኢህአዴግ ፣ የኢትዮጵያ ህዝብና ወያኔ !!

## መግቢያ ፣

የግንቦት ስምንቱ ምርጫ ከተካሄደና ውጤቱም ተጭበርብሮ ኤህአዴግ በወጭ ኃይል እየታገዘ አምባ ገነናዊ አገዛዙን አጠናክሮ ህዝባችንን ሲጨፈጭፍና አገር ሲያተራምስ ይኸው አንድ ዐመት ሊጠጋው ነው። በጊዜው ምርጫው ሲካሄድና ያልተጠበቀው ውጤት ቢገኝም ፣ በሌላ ወገን ግን ኢህአዴግ ከምርጫው በፊት በተለያዩ መንገዶች ይፎክር የነበረውን "ስልጣን ተዋግታችሁና አሸንፋችሁ ውሰዱ" በሚለው ኋላ ቀር አባባሉ ገፍቶ በህዝባችን ላይ እንደዚያ የክህደትና የጭፍጨፋ እርምጃውን ይገፋበታል ብሎ ያሰበ አልነበረም። ቢያንስ ለጊዜው ከስልጣን አልወርድም ብሎ ቢንገዳገድም የኋላ ኋላ መሸነፋን አምኖ "በሰለጠነ" ሁኔታ ስልጣኑን ህዝቡ ለመረጣቸው መሪዎች በማስረከብ የተቃዋሚ ሚናውን እየተጫወተ አዲስ ታሪክ ይጽፋል የሚል እምነት በአንዳንዶቻችን ዘንድ እንደነበር የማይካድ ሀቅ ነው። በሌላ ወገን ደግሞ ይህንን ምርጫ እንደ ታሪካዊ ብቻ ሳይሆን ለዲሞክራሲያዊ ግንባታ አንድ እርምጃ አድርገው በቆጠሩና ምርጫው ተጭበረበረም አልተጭበረበረም ተቃዋሚው ኃይል የግዴታ ፓርላሜንት ውስጥ ገብቶ ሁኔታዎችን ለተቀጣዩ ምርጫ ማመቻቸት አለበት በሚሉ መሀከል ግልጽ ያልሆኑ እጅግ መሰረታዊ የዲሞክራሲያዊና የነፃነት እንዲሁም የኢኮኖሚ ግንባታ ጥያቄዎች እንዳሉ በፍጹም የማይካድ ጉዳይ ነው። እነዚህ አቀንቃኝ ኃይሎችና ዓለም አቀፋዊ ኮሚኒቲው የሚባለው ከምርጫው በኋላ ለተከሰተው ግድያና ብጥብጥ አገዛዙን ሳይሆን አሁንም ቢሆን ህዝብ የመረጣቸውን መሪዎችና ውጭ አገር የምርጫውን መጨበርበር አስታኮ በአገር ፍቅርና ወዳድነት ሳያቋርጥ የተቃውሞ ድምጹን የሚያሰማውን የበሰለና ቆራጥ ኃይል በመወንጀል ነው።

የግንቦቱ ምርጫ ታሪካዊ የሆነውን ያህል ፣ ምርጫው  የአስራ አራት ዐመቱን የኢህአዴግ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ፣ በብሄረ-ሰቦች ነፃነት ስም አስታኮ አገራችንን በድብቅና በይፋ ህልውናዋን ማዳከም ፣ በነፃ ገበያ ስም እየነገዱ ኢኮኖሚውን በተወሰኑ ሰዎች ቁጥጥር ስር ማዋልና ድህነትን መፈልፈል ፣ እንዲሁም የአገራችን ዕድገትና ስልጣኔ የሚያግዙና የሚጠቅሙ ሳይሆን ፣ የኢኮኖሚውን ሂደት አዛንፈው ህዝባችን የተዝረከረከ ኑሮ እንዲኖር የሚያደርጉ እንደቅኝ ገዢዎች የሚፈላሰሱ ከ250 000 በላይ የሚቆጠሩ ብሄራዊ ነፃነታችንን የሚቀናቀኑ የውጭ ኃይሎችን ሚና በፍጹም ሊሸፍነው አይችልም። የምርጫው መፈቀድና መካሄድ የኢህአዴግን ውስጣዊ ዲሞክራሲያዊ ግንዛቤና አምባገነናዊ ባህርዩን ከቶም ሊደብቀው አይችልም። ኢህአዴግ አስራ አራት ዐመት ያህል ዲሞክራት ያልሆነውን ያህል ምርጫውን ስለፈቀደ ከመቅጽበት ዲሞክራት ሊሆን የሚችልበት አንዳችም ተዐምር የለም።የምርጫው መጭበርበርምና አስከዛሬ ድረስ በህዝባችን ላይ የሚካሄደው ቅጥ ያጣ ጭፍጨፋና አፈና ይህንን ነው ያስመሰከረው። ኢህአዴግ ዲሞክራት ያለመሆኑን ፤ ዕውነተኛና ህዝብን የሚጠቅም ሁለ-ገብ የአኮኖሚ ዕድገትን ለማየት የማይፈልግ መሆኑን ዛሬ ለማንም ግልጽ የሆነበት ወቅት ነው።

ከዚህ መሰረታዊ ሀቅ በመነሳት የኛን ምኞትና ህልም ፣ እንዲሁም አገራችንን ገነት ማድረግና የሳይንስና የቴክኖሎጂ ባለቤት እንድትሆንና ህዝባችን እውነተኛ ነፃነቱን እንዲቀዳጅ ከምናደርገው ትግል አኳያ የኢህአዴግን የጨለማና የጥፋት ጉዞ ጋር እያነፃፀርን በማስቀመጥ ዛሬ ጠቅላላው ኢህአዴግን የሚዋጋው ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆነው ኢትዮጵያዊው ኃይል የሚመኘውን ፣ በጭንቅላቱ የሚያብሰለስለውን ፣ አገሩ በድህነት እየተጠራች ስትኖር የሚቆጨውን ወደ ውጭ አውጥተን ኢህአዴግም ሆነ አጋሮቹ እንዲረዱት የማድረግ ታሪካዊ ግዴታ አለብን። በዚህም በዚያም ብለው እኛን በስልጣን ጥም የሚከሱን ፣ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ስማችንን የሚያጠፉት ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚመኘውን እንዲያውቁትና እን

ዲገነዘቡት ግዴታችን ነው። የኛ ትግል ቅራኔዎችን ማባባስ ሳይሆን ምራቅ የዋጠና በዚያች በአገራችን ምድር ህዝባዊ ስምምነትና ፍቅር ዳብረው ሁሉም በጋራ አገሩን እንዲገነባ የሚያደርግ እውነተኛ ነፃነትን ከመፈለግ ከልብ የመነጨ ስሜት መሆኑን ለጠላትም ሆነ ለወዳጅ ለማረጋገጥ ነው።

## የኛ ዲሞክራሲ ለወያኔና ለግብረአበሮቹ የእሳት ወላፈን

ለጠላቶቻችንም ሆነ ለወዳጆቻችን እስካሁን ግልጽ ያለሆኑ መሰረታዊ ጉዳዮች አሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ዲሞክራሲና ዲሞክራሲያዊ ክንውኖች ከእውነተኛ የጭንቅላት ነፃነት/ኢማንሲፔሽን/ ጋር በጥብቅ የተያዙ ናቸው። ዲሞክራሲያዊ መብት በመጻፍና በመተቸት ወይም በሰላማዊ ሰልፍ ብቻ የሚገደብና ፓርላማ ውስጥ የተቀመጡ የህዝብ ተወካይ ነን ባዮች ፣ የህዝብ ተመራጮች ነን በሚል በህዝብ ስም የሚመጻደቁበትና የተከበሩ እየተባሉ ከህዝብ ተገልለው በየአራት ዐመቱ ለምርጫ የሚቀርቡበት ልዩ ክንዋኔ አይደለም። ዲሞክራሲያዊ መብትና ክንዋኔ በአንድ አገር የሚኖር ህዝብ ፍላጎት ፣ ምኞትና ተፈጥሮአዊ ነፃነት ተግባራዊ የሚሆኑበት ልዩ ዐይነት ታሪካዊ መስሪያ መሳሪያ ነው። ዲሞክራሲያዊ መብት ፣ ፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ ፣ ባህላዊ ፣ የህብረተሰብ እሴትና የኢኮኖሚ ዕድገት ተግባራዊ የሚሆኑበት ፣ የጠቅላላው ህዝብ ምኞት የሚንፀባረቅበትና ይህ ምኞቱም የሚሟላበት ፣ ለዚህ ወይም ለዚያኛው መደብ ብቻ ተቆጥቦ የሚሰጥ ሳይሆን የትንሹም የትልቁም ተፈጥሮአዊ መብቱ መግለጫ ነው።

ይህ ዐይነቱ የዲሞክራሲ ግንዛቤ ከተራ የፓርላማ ውክልና የሚለይበት መሰረታዊ ጉዳዮች አሉ። የፓራላማው ዲሞክራሲ ቀጥተኛ ህዝባዊ ተሳትፎን የሚቃወም ሲሆን ፣ ተጠሪዎች ለመረጣቸው ህዝብ ቀጥተኛ ተጠያቂዎች አይደሉም። በፎርማል ደረጃ የሚካሄድ በመሆኑ የግዴታ እንደ ኢትዮጵያ ላለው ፣ በብዙ ነገሮች ለተጎዳ ህዝብና በብዙ ሚሊዮን ችግሮች ለተተበተበ መሰረታዊ ችግሩን ሊፈታና በፀና መሰረት ላይ እየተጓዘ ሳይንስና ቴክኖሎጂን እን ዲቀዳጅ ሊያደርገው በፍጹም አያስችለውም። ይሁንና የፎርማሉን ዲሞክራሲና እውነተኛ በህዝብ ዘንድ ተጠያቂነትንና ፍላጎትን ተግባራዊ የማድረግ ጉዳይ አንድ ላይ ሊሄዱ የማይችሉበት ምንም ምክንያት የለም። እንደዚህ ዐይነቱ ቀጥተኛና ፎርማል ዲሞክራሲ በአን ድ ላይ ሊጣመሩ የሚችሉት በአንድ በኩል በህዝብ ዘንድ ለዕድገትም ሆነ ለዕውነተኛ የነፃነት ኑሮ ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንደ አየርና ውሀ እንዲሁም ምግብ አስፈላጊ መሆናቸውን ግንዛቤ ውስጥ ሲገባ ነው። በሌላ ወገን ደግሞ የህዝብ ተወካይ ለመሆን ለሚሹና የህዝብን ፍላጎት በፓርላማ አማካይነት ማሟላት ይቻላል ብለው በሚታገሉ ኃይሎች ዘንድ እውነተኛ የጭንቅላት ነፃነትን ተጎናጽፎ ከህዝብም ሆነ ተቃዋሚ ነኝ ከሚለው ኃይል ዘንድ የሚሰነዘረውን ትችት እንደስድብ ሳይሆን እንደ አውነተኛ የአገር ግንባታ መታገያ መሳሪያና ተቻችሎ ለመኖር አስፈላጊ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ሲገባ ብቻ ነው። ህብረተሰባዊ ትችት በሌለበት ፣ ህብረተሰብአዊ ትችቶች በሙዚቃ ፣ በአርክቴክቸር ፣ በስዕል ፣ በኢኮኖሚ ዕድገት በማይገለጽበት ሁኔታ ውስጥና በነዚህ መሰረት የህዝብ ፍላጎት በማይሟላበት አገር ስለዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበርና ህዝባዊ ተሳትፎ እንዲሁም የአገር ግንባታ ማውራት በፍጹም አይቻልም።

የዲሞክራሲ መብት የግለሰብን ነፃነትና የፈጠራ ድርጊት ያካተተ ፣ ካለግለሰብ ነፃነት ተግባራዊና ውጤታማ ሊሆን እንደማይችል የተረጋገጠ ነው። ከሶስት ሺህ ዐመት በፊት ለዲሞክራሲና ለነፃነት ትግል ሲጀመር አነሳሱም ግለሰብአዊ ነፃነትን ከዲሞክራሲያዊ ትግልና ከዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ጋር በማያያዝ ነው። በጊዜው የግለሰብ ነፃነት ከፍተኛ ቦታ ተሰጥቶት ትግል ሲጀመር ፣ ዕውነተኛ የግለሰብ ነፃነት ካልሰፈነ አንድ ግለሰብም ሆነ ህብረተሰብ የመፍጠር ችሎታው እንደሚታፈንና በተፈጥሮ ኃይል መናጋት የሚከሰቱም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋዎች ለመቋቋምና ወደፊት እንዳይከሰት አዳዲስ መሳሪያዎችንና የመከላከያ

ሆኔታዎችን ለመፍጠር እንደማይቻል በመገንዘብ ነው። ስለዚህም ማንኛውም ግለሰብ እኩል
የተፈጠረ ስለሆነና በእግዚአብሔርም ሆነ ከህግ በፊት እኩል ስለሆነ ዲሞክራሲና ግለሰብአዊ
የነፃነት ጥያቄዎች በተወሰኑ ሰዎች ወይም ቡድን ተቆጥበው የሚሰጡ ሳይሆን ተፈጥሮአዊ
መብቶች መሆናቸውን በመገንዘብ ነው ትግሉ የተጀመረው። ግለሰብአዊና ህብረተሰብአዊ
ነፃነት እንዲሁም የዲሞክራሲ መብት ጥያቄዎች ተደጋግፈውና ተያይዘው የሚሄዱ ሲሆን ፣
የየግለሰቦች የነፃነት አጠቃቀምና አተረጓጎም ጉዳይ በአንድ በህብረተሰብ ውስጥ ባለው
የዕውቀት ሁኔታና ደረጃ ፣ እንዲሁም ደግሞ በየጊዜው መሻሻል ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው።
በሌላ አነጋገር የዲሞክራሲና የነፃነት ጥያቄ ተፈጥሮአዊ መብትን ብቻ ሳይሆን ግዴታንም
ያካተተ ነው። በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ የሚኖሩ ግለሰቦች ተመሳሳይ የዕወቀት ደረጃ
የላቸውም።የዲሞክራሲንና የነፃነትንም ጥያቄ እንደፈለጉት ሊተረጉሙት ይችላሉ። ይህ
ችግር እንዳይፈጠር ሁሉም በህግ ፊት መብት ያለው ብቻ ሳይሆን ግዴታም እንዳለበት እን
ዲረዳው የህግ መኖርና የዲሞክራሲ ጥያቄዎችና የግለሰብ ነፃነቶች በግለሰብም ሆነ በመን
ግስት ኢንስቲቱሽኖች ሲጣሱ ለመቆጣጠርና ፊር ለማስያዝ የህግ የበላይነት መኖር
አሰፈላጊነት ጉዳይ ግንዛቤ ውስጥ የተገባውና ትግልም የሚደረገው። ዲሞክራሰያዊ
መብቶችና የግለሰብ ነጻነቶች ሲጣሱ ፣ መጣሳቸውን የሚከታተል ከአንድ አገዛዝ መደብ
ውጭ የሆኑ ኢንስቲቱሽኖች ከሌሉ የህግ በላይነት ተግባራዊ ለሆን አይችልም። ስለሆነም
በኤክስኩቲብና በህግ አውጪ እንዲሁም ደግሞ በህግ አስፈጻሚው ኢንስቲቱሽኖች መሀከል
ግልጽ የሆነ የአሰራር ክፍፍልና ጣልቃ ያለመግባት ፣ የዲሞክራሲያዊ መብቶችና የግለሰብ
ነፃነቶች ፖለቲካዊ ጫና እንዳይገጥማቸው ከመጀመረያውኑ በግልጽ መቀመጥና መከበር
ያለበት ጉዳይ ነው።

የዲሞክራሲያዊ መብቶችና የግለሰብ ነፃነት ተግባራዊነት በፓርላሜንት ውስጥ በሚካሄድ
ተሳትፎትና ክርክር አልፎ የሚሄድ ፣ በልዩ ልዩ መንግስታዊም ሆኑ መንግስት-ነክ ባልሆኑ ኢን
ስቲቱሽኖች አማካይነት ሊሟላና የህዝብ ፍላጎት ፍጻሜ ሊያገኝ የሚችለው። ዲሞክራሲያዊ
ኢንስቲቱሽኖች በሌሉበት ፣ አገዛዝና መንግስት ግልጽ የሆነ የስራ ክፍፍላቸው ባልታወቀበት
አገር ፣ አንድ የገዢ መደብ ኃይሉን ተጠቅሞ መንግስታዊ መዋቅሮችን ፣ ማለትም ፍርድ
ቤትን ፣ ፖሊስንና የጸጥታ ኃይልን እንዲሁም የወታደርንና የሲቪል በሮክራሲያዊ መወቅሮችን
ለራሱ የመጨቆኛ መሳሪያ የሚጠቀምበት ከሆነ ስለ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ተግባራዊነት
በፍጹም ማውራት አይቻልም። እነዚህ አካሎች የህዝብን መብቶች ማስጠበቂያ እንጂ ማንም
ኃይል የራሱ አገዛዝ መሳሪያ ሊያደርጋቸውና ከህገ-መንግስት ውጪ በመጠቀም ህዝብን እን
ደፈለገ የሚረግጥበትና የሚያስፈራራበት ሊሆን አይገባውም። ህዝብና መንግስታዊ መዋቅሮች
እንደጠላት የሚተያዩበት ሳይሆን ፣ የአንድ አገር አካሎች ፣ በመከባበርና በመፈቃቀር በጋራ
አገር የሚገነቡበትና የሚፈላለጉ ፣ አንደኛው ከሌላው ተነጥሎ በፍጹም ሊኖር እንደማይችል
በዲሞክራሲ መብት የሚገለጽ መሆን አለበት። ይህ ዐይነቱ በመንግስት መዋቅርና በህዝብ
መሀከል ሊኖር የሚችለው መፈላለግና መተማመን በየጊዜው የሚዳብር ፣ በልዩ ልዩ የጭን
ቅላት ገንቢ ትምህርቶች የሚጠነክርና የሚተሳሰር ሲሆን ፣ ለአገር ግንባታና ለህዝብ
መተሳሰርና መከባበር አስፈላጊነቱ የበለጠ ግንዛቤ ውስጥ እየገባ ይመጣል። በዚህ መልክ
ብቻ ነው አገዛዝ ፣ መንግሰትና ህዝብ የአንድ አገር አካል ሆነው በጋራ እጅ ልጅ ተያይዘው
በህብረተሰብአዊ ስምምነት ታሪክን ሊሰሩና ለመጪው ትውልድ ሊያስተላለፉ የሚችሉት።

ለእንደዚህ ዐይነቱ የዲሞክራሲያዊ መብትና ለግለሰብ ነፃነት ተግባራዊነት እንዲሁም
ለህብረተሰብአችን ዕድገት ትግል ከተጀመረ ከአርባ ዐመት በላይ ሊሆነው ነው። በጊዜው
በነበረው የዘበራረቀ ሁኔታና በአንድ በኩል የዲሞክራሲ መብቶች መኖርና አስፈላጊነት
መረዳት ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ይህንንን መብት በሰፊው በመረዳትና ማንኛውንም
ህብረተሰብአዊ ችግሮች በግልጽ ውይይት መፍታት ያስፈልጋል ፣ ስለዚህም በመንግስት ኢን
ስቲቱሽኖችና በህብረተሰብ ውስጥ የነበረውን የትምህርት ሁኔታ በቅጡ መረዳት ያስፈልጋል
በሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ላይ ቀድሞውኑ ውይይት ሊደረግ ባለመቻሉ ፣ የተማሪው እን
ቅስቃሴ ይዞ የተነሳቸው የዲሞክራሲዊ መብት ጥያቄዎች ተግባራዊ ለመሆን ተሳናቸው።
የስድሳ ስድስት የየካቲት አብዮት ሲፈነዳ ፣ አብዮቱ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ

የመጀመሪያው ታሪካዊ ክስተትና የማይታለፍ ጉዳይ ቢሆንም የተማሪው እንቅስቃሴ የዲሞክራሲ ጥያቄ የገጠመው ችግር የህብረተሰቡን የህሊና አወቃቀር ፣ የባህል ሁኔታና የልዩ ልዩ ኢንስቲቱሽኖችን የዕድገት ደረጃ በቅጡ ባለመገንዘቡም ሆነ ለመረዳት ባለመሞከር ወይንም ዝግጁ ለመሆን ባለመቻል ሊከሰት የማይገባው ሁኔታ ተፈጠረ። የዲሞክራሲ መብቶች ጉዳይ በውይይት የሚፈታ ፣ ለአንድ ህብረተሰብ ዕድገት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ፣ መደማመጥና መቻቻል ለዲሞክራሲ መብቶች ማበብና መዳበር ግንዛቤ ውስጥ አለመግባት ህዝባችን የሚመኘው የዲሞክራሲና የግለሰብ ነፃነት ተግባራዊ ሊሆን አልቻለም። በጊዜው በተሳሳተ መልክ የዲሞክራሲያ መብቶችን ተግባራዊነት ጉዳይ የግዴታ ከአመጽ ጋር ለማያያዝ በመሞከሩ ፣ የዲሞክራሲ መብት መከበር የግዴታ በጠበንጃ አፈሙዝ ብቻ ተግባራዊ መሆን ያለበት መሆኑን ጭንቅላት ውስጥ ስለተቀረጸ ፣ የግዴታ እንደዚህ ዐይነቱ የተሳሳተ አመለካከት ለተለያዩ ኃይሎች ለአመጽ በር ከፈተላቸው። በሌላ ወገን ደግሞ በየካቲቱ ወቅት የተፈጠረው የተቃወሰና ዝብርቅርቅ ሁኔታ የዲሞክራሲንና የግለሰብን ነፃነት መኖርና መከበር ከስልጣንና ከጥቅም ባሻገር ማየት ላልቻሉ ኃይሎች የወቅቱ የኃይል አሰላለፍ በስልጣን ላይ ብቻ እንዲያተኩሩና የህዝብን ፍላጎት በመርገጥ ለዲሞክራሲ መብቶች መከበርና ለግለሰብ ነፃነት በሚታገሉ ኃይሎች ላይ ከገዢው መደብ ጋር በማበር ተረባረቡባቸው። የየካቲቱ አብዮት የኋላ ኋላ አጅግ አድርባይና ለስልጣን የቋመጡና ዕድላቸውን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ሳይሆን ከውጭ ኃይሎች ጋር ያቆራኙ ጉድ ፍጡሮችን ፈለፈለ። ሺህ በሺህ የሚቆጠሩ እነዚህ ጉዶች ለጊዜያዊ ጥቅም በመታወርና በመገዛት የነፃነቱን ትግል አዳፈኑት። ያማያሰፈልግ ሽኩቻንና አፈናን በማስፋፋት ህዝባችን በፍርሀት እንዲዋጥና የኑሮው ፍልስፍናውም ለነዚህ ጉዶችና ለገዢው መደብ እያሸረጎደ እንዲኖር የተደነገገበት ፍጡር ሆነ። ተፈጥሮአዊ መብቱ በመረገጡና የፈጠራ ችሎታውም በመታፈን በግልጽ የሚያያቸውን ችግሮች ሊፈታና ዕድገትን ሊያመጣ አልቻለም። ዕጣው ረሀብና የሰውን እጅ እያየ እንዲኖር ተገደደ።

ወያኔ ወይም ኢህአዴግ በውጭ ኃይሎች እየታገዘ ስልጣን ሲይዝ በየካቲቱ ወቅት የተበላሸውን የዲሞክራሲ መብት ጥያቄ አፈታት ለማስተካከል ሳይሆን ለራሱ በሚመቸው መልክ በማዘገጀት ህብረተሰቡን ለመበወዝና ፣ ሀይማኖትን ከሀይማኖት ፣ ብሄረ-ሰብን ከብሄ-ረሰብ ጋር በማጋጨት ስልጣኑን ለዝንተ-ዐለም ለማደላደል አመቺ ሁኔታን ፈጠረ። በአስራ አራት ዐመት የኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን ትንሽ የዲሞክራሲ ጭላንጭል ቢታይምና አንዳን ዶቻችንም ይህንን ቀዳዳ ተጠቅመን ህዝባችን የከፋፋዮች ሰለባ እንዳይሆን ለመጠቆም ብን ሞክርም የኢህአዴግ ዲሞክራሲ እራሱ ከሚፈልገው የዲሞክራሲ ዐይነት ተሻግሮ መሄድ እን ደሌለበትና በብዙ ተንኮሎች የተጠላለፈ ፣ ለዕውነተኛ ነፃነት እንቅፋት የሆነና አገራችንን ከፍተኛ አደጋ ውስጥ የከተተ እንደነበር ሁላችንም የተረዳነው ነው። በኢህአዴግ ዲሞክራሲ በተወሰነው የህብረተሰብ ክፍል የጭንቅላት መዳበር ሳይሆን ከፍተኛ ብልግና የተከሰተበትና የህዝባችንን ባህል ሳይንሳዊ ሳይሆን ብልሹ ያደረገና ፣ በተለይም ደግሞ ወጣቱን ለወጭ የቆሻሻና አገር አፍራሽ ባህል አደጋ ውስጥ የከተተና ያጋለጠ ነው።

ከግንቦቱ ስምንት ምርጫ በፊት የተካሄዱት ውይቶችና ክርክሮች በህዝባችን ውስጥ ታምቆ የነበረውን ዕውነተኛ የዲሞክራሲና የግለሰብ ነፃነት ፍላጎት ወደ ውጭ ያወጣና ፣ ይህም ፍላጎት ምርጫው ከመካሄዱ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ በተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍና በምርጫው ወቅት በግልጽ የታያና ከዚያን ገዜ ጀምሮ ህዝባችን ለከፋፋይ ኃይሎች የማይታለል መሆኑን ያረጋገጠበት ነው። ኢህአዴግንም በምርጫ አሽቀንጥሮ ሲጥለው የኢህአዴግንን ምንነት በቅጡ መገንዘቡ ብቻ ሳይሆን ፣ዕውነተኛ ዕድገት ሊመጣ የሚችለው ራሱ ህዝቡ ዲሞክራሲዊ ተሳትፎ ሲኖረውና ራሱ በመረጣቸው ተወካዮች ሲተዳደር ብቻ መሆኑን በሚገባ በመገንዘቡ ነው። ይህንን ጉዳይ ኢህአዴግም ሆነ የሙጥኝ ብለው ኢህአዴግን የሚደግፉ  የውጭ ኃይሎች የተገነዘቡት ይመስለል። ኢህአዴግም ሆነ የውጭ ኃይሎች በአስመሳይነት የግንቦት ስምንቱን ምርጫ ሲፈቅድና ሲደግፉ የህዝባችን ንቃተ-ህሊና እስከዚህ ድረስ ገፍቶ የሄደ መስሎ አልታያቸውም ነበር። ተግባራዊ ባደረጉት የተወላገደና አፍራሽ የነፃ ገበያ ፖሊሲ ህዝባችን በሀሳብ ተበታትኖ የሚቀር እንጂ እንደዚህ

የሚያስተሳስረው ውስጣዊ ኃይልና ታሪክም ሆነ ባህል ያለው መሆኑን በቅጥ የተገነዘቡ አይመስሉም። በምርጫ አታለን ለሌላ አምስት ዐመት ሰቆቃውን እናረዝመዋለን ፤ የብዝበዛውንና የድህነቱን ዘመን እናራዝመለታለን ብለው ተማምነው ነበር። ይህ የተበላሸና እርኩስ የፖለቲካ ስሌታቸው ግን በፍጹም ሊሰራ አልቻለም። እነሱ ካሰቡት በላይ የህዝባችን ንቃተ-ህሊና ቀድሞ የሄደና ፍላጎቱም በተወላገደና በሚሸመደመድ ዲሞክራሲ ሊሟላ እን ዳማይችል መገንዘቡን በፍጹም የተረዱ አይመስሉም።

ከሰኔው አንድ ጭፍጨፋ ጀምሮ በህዝባችን ላይ የሚካሄደው ቅጥ ያጣ አፈና ፣ ግድያና አሰራ ፣ እንዲሁም ደግሞ ቅንጅትን ለመበታተንና ለማዳከም ግልጽና ድብቅ ሴራ ማካሄድ ዕውነተኛ ዲሞክራሲ በአገራችን ምድር እንዳያብብ ፣ ህዝባችን የእውነተኛ ነፃነት ባለቤት እን ዳይሆን ለማድረግ ከተተለመው የረጅም ጊዜ ዕቅድ ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው። ወያኔም ሆነ የውጭ ኃይሎች በራሱ የሚተማመንን ፣ በዕውነተኛ ነፃነት ታጅቦ የተከበረችና ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያን የሚገነባ ኩሩና ታሪክን ለመስራት የሚነሳ ህዝብ ማየት አይፈልጉም። እነሱ ማየት የሚፈልጉት ዲሞክረሲ ፣ ታሪክን የማያሰራ ፣ ህዝብን የማያስከብር ፣ ብሄራዊ-ነፃነትን የሚያስደፍርና ክርክር ውስጥ የማያስገባና ጥያቄ እንዳን ጠይቅ የሚያደርግ ዲሞክረሲ ነው። ሳይንስንና ቴክኖሎጂን የሚጻረር ፣ እንዲሁም ደግሞ ለእነሱ ብዝበዛ የሚያመች ዲሞክራሲን ነው የሚሹት። ለዚህም ነው ዛሬ ወያኔን አማራጭ እንደሌለው ኃይል ባለ በሌለ ኃይላቸው የሚደገፉትና በህዝባችን ላይ የሚያሴሩት። የህዝባችን የዲሞክራሲ ጥማት ለእነሱና ለወያኔ የእሳት ወላፈን መሆኑን በመገንዘባቸው ህዝባችን የሚፈልገውን ዲሞክራሲያዊ መብትና የግለሰብ ነፃነት ከማየት ይልቅ የተበታተነች ኢትዮጵያን ማየት ደስ ይላቸዋል። ለኛ ለሀቀኛ የህዝብ ወገኖች ፣ በውጭም ሆነ በአገር ቤት ውስጥ የቅንጅትን አርማ ይዘን ለምንታገል ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ይህ የውጭ ኃይሎች ሴራ ከምን ጊዜውም የበለጠ ግልጽ እየሆነልን መጥቷል። ትግሉም ከወያኔ ጋር ብቻ ሳይሆን ከውጭ ኃይሎች ጋር እየሆነ በመምጣት ላይ ነው። አዝማሚያውም ወደዚያ የሚያመራ ይመስላል።

በዛሬው ወቅት ፣ ህዝባችን የተነጠቀውን የምርጫ ውጤት ለማስከበር ከገዢው መደብ ጋር የሞት የሽረት ትግል በሚያደርግበት ወቅት ፣ የየካቲቱ ሁኔታ እየተደገመ ነው። በስልጣን ጥም የሰከሩ ፣ የህዝብ ፍላጎትና ነፃነት የማይታያቸው ፣ ዕውነተኛ ዕድገትን የሚፃረሩ አድርባይ ኃይሎች ከውጭ በሚጣልላቸው ፍርፋሪና በስልጣን በመታለል በህዝባችን ላይ ከገዢው መደብ ጋር አብረው የሚያካሂዱት ዐይን ያወጣ ሴራ እጅግ አሳፋሪ መሆኑን መገን ዘብ ያስፈልጋል። እንደዚህ ዐይነቱ አድርባይነት የባህላችን አንድ ጎን እየሆነ በመምጣትና ህዝብን በማተረማመስ የነፃነትን ፍላጎት ማራዘም ተደጋጋሚ እየሆነ በመምጣት ላይ ነው። እኛ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎችና የህዝብ ወገኖች ይህንን በየጊዜው በህብረተሰብአችን ውስጥ በጥቂት ግለሰቦችና ቡድኖች ከአንዴም ሁለቴም የተከሰተውን አድርባይነት አደገኛነቱን ተረድተን ታሪካችንን መመርመር እንዳለብን ከአሁኑ ግዴታችን መሆኑን መረዳት እንዳለብን መገንዘብ ይኖርብናል። በአንድ አገር ውስጥ በሚገኝ የምሁር ህብረተሰብ ክፍል ውስጥ የተለያየ አስተሳሰብ ሊኖር ቢችልም ፣ ልዩነቱ ግን በሀሳብ ዙሪያ የሚሽከረከር እንጂ አድርባይ ባህርይ ይዞ ትግልን የሚያኮላሽና አገርን ወደመበታተን ለማምራት የሚቃጣ መሆን የለበትም። የአንድ አገር ምሁር ታሪካዊ ኃላፊነት ታሪክን መስራት መሆኑን ተገንዝበን ፣ ለእንደዚህ ዐይነቱ ቅጥ ያጣ አድርባይነት በምንም ዐይነት ቀዳዳ መስጠት የለብንም። የዕውነተኛ ዲሞክረሲያዊ መብቶች መከበርም ጉዳይ በሀሳብ ዙሪያ የሚሽከረከር ክርክርና ውይይት መሆኑን ተረድተን አድርባይነትን መዋጋት ታሪካዊ ግዴታችን ነው።

## የኛ ፖለቲካ ህብረተሰብአዊ ስምምነትንና ፍቅርን ፣ የወያኔ ፖለቲካ ትርምስን

ዛሬ እኛን አጥብቀው የሚዋጉና በዚህም በዚያም ብለው የህዝባችንን ትግል አኮላሽተው የወያኔን አገዛዝ ዘመን ለማራዘምም ሆነ በጅምላ በፀረ-ትግሬነት የሚወነጅሉን ኃይሎችም ሆነ ራሱ ወያኔ ያልተገነዘቡት አንድ ነገር አለ። ይኸውም ፖለቲካ ሲባል ለጥቂት ኃይሎች የተሰጠና ህዝብን ማተረማመሻ መሳሪያ እንጂ ፣ ፖለቲካ ሲባል አንድን ህብረተሰብንና አገርን ለማስተዳደርም ሆነ ለመጠበቅ የሚያስችል ልዩ ጥበብንና ስልት ያዘለ ሳይንሳዊ መሳሪያ ያለመሆኑን ነው። እነዚህ ኃይሎችም ሆነ ወያኔ ራሱ ጭፍን ካልሆኑ በስተቀር አንድ ህብረተሰብ ባለፉት አስራ አራት ዐመታት በተካሄደው ዐይነት ፖለቲካ እንደ ህብረተሰብ ሊገነባና ለመጪው ትውልድ ሊተላለፍ እንደማይችል ነው።

በአገራችን ምድር ውስጥ በተለይም ከደርግ አገዛዝ ወዲህ አንድ የተለመደ መጥፎ ባህርይ አለ። ፖለቲካ መሸወጃና የራስን ጥቅም ማስጠበቀያ ፣ እንዲያም ሲል ከዚህኛውም ሆነ ከዚያኛው ኃይል ጋር በአድርባይነት በማበር ስልጣን ላይ ቁጥጥ ለማለት መታገል ነው። ይህ ዐይነቱ የተበላሸ አመለካከትና ፍልስፍና በወያኔ ዘመንም በለዩ መልክ በመቀጠልና ህዝብን በማተረማመስ ላይ ይገኛል። የወያኔው የፖለቲካ ፍልስፍና ከደርጉ የሚለየው ፣ አውቆና በስሌት የሚካሄድ ሲሆን ፣ የደርጉ ግን አገርን ለማፈራረስና ህዝብን ለማተረማመስ ሆን ብሎ የተጠነሰስና የተዘጋጀ ያለመሆኑ ነው። የወያኔ የአጭር ዘይቤ ፖለቲካም በመሰረቱ በንቀትና ኢትዮጵያዊነትን በመካድ ላይ የተገነባ ሲሆን ፣ ከመጀመሪያውኑ የውጭ ኃይሎች ቡራኬ ያለበትና ካለውጭ ኃይሎች ድጋፍ በትርምስ ፖለቲካው ሊገፋበት እንደማይችል ያረጋገጠ ነው። ይህ ዐይነቱ ፍልስፍና አልባ የሆነ ፣ ከዚህኛውም ሆነ ከዚያኛው  የፖለቲካ ፍልስፍና ስልት ውስጥ የማይገባ ፣ መሰረቱ በአወቅሁኝ ባይነት ፣ በአመጽና በአራዳነት ወይም በጮሌነት ላይ የተገነባ የፖለቲካ ስሌት ህዝብን የሚያርቅና ህዝብን ለስራና ለፈጠራ ድርጊት አዘጋጅቶ በጋራ አገር እንዲገነባ የሚያግዝ የፖለቲካ ዘይቤ እንዳይደለ አስራ አራት ዐመት የተካሄደው ፖለቲካ በግልጽ አረጋግጧል።

አስራ አራት ዐመት ያህል እንደተከታተልነው ፣ ህብረተሰቡ ስምምነትና ፍቅር እንዳይኖረው በክልል ፖለቲካ የኋሊት ጉዞ ተጉዞ የዘመነ መሳፍንት ዐይነት እዚህና እዚያ የተበጣጠሰ በራሱ ክልል ብቻ የሚሽከረከር አገዛዝ እንዲዋቀር ተደርጎለታል። በህብረ-ብሄር ግንባታና የአገዛዝ ዘመን የአንድን አገር አገዛዝ አፍርሶ ህዝባችን የኋሊት ጉዞ እንዲጓዝ ማድረግ በዓለም ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ሳይሆን እንደማይቀር የተረጋገጠ ነው። በወያኔ የክልል ፖለቲካ ስንትና ስንት ሺህ ህዝብ ከየአካባቢው እንደተፈናቀለ ፣ በጥቂት ከተሞች እየተሰገሰገ እንዲኖርና ፣ በከተሞች ውስጥም ሌላ ጭንቀትና ትርምስ እንዲሁም ደግሞ በቀላሉ መፍትሄ የማይገኝለት የባህልና ህብረተሰብአዊ ቀውስ እንደተፈጠረ ዛሬ ለማንኛችንም ግልጽ ነው። ይህ ዐይነቱ ህብረተሰብአዊ አለመረጋጋትና ፣ ህዝቡ በሚያውቀው በዚያው በአካባቢው ተረጋግቶ አለመኖር ምናልባት ለወያኔና ለግብረ አበሮቹ ፣ እንዲሁም ዛሬ እኛን ኢትዮጵያ ውስጥ ለተፈጠረው ቀውስ እንደተጠያቂ አድርገው የሚቆጥሩን ኃይሎች አንድ ግልጽ ያልሆነላቸው ነገር አለ። ይኸውም አንድ ህብረተሰብ እንደህብረተሰብ እንዲኖር ከተፈለገ በአንድ የተወሰነ የፖለቲካ ፍልስፍና መመራት እንዳለበትና ለዚህም ደግሞ ሃሳቡ ተንጠልጥሎ ሳይሆን በረጋ መንፈስ ታሪክን ሊሰራ የሚችል ኃይል ሆኖ ከላይ ከሚጫንበት ፖለቲካ ተላቆ ማንነቱን ሊገልጽ የሚችልበት ስርዐት ሲዘጋጅለትና ካለፍርሀት ሲንቀሳቀስ ብቻ ነው። ይህ ዐይነቱ ፖለቲካ ፣ ህዝብን የሚያስተሳስርና ለስራ የሚቀስቅስ እንዲሁም ደግሞ ወደ ኃይል ተለውጦ ለወጭ ኃይል አንገቱን አቀርቅሮ እንዲገዛ የማያደርግ ፖለቲካ ወያኔንም ሆነ የውጭ ኃይሎችን ያስፈራቸዋል። ምክንያቱም የተሳሰረና የተፈቃቀረ ህዝብ እንዲሁም በዲሞክራሲያዊ መርሆች ላይ የተዋቀረ ፖለቲካ የአንድን ህብረተሰብ የመፍጠር ችሎታ ያዳብራልና።

የኢህአዴግን የብሄረ-ሰብ መብት ተግባራዊነት ስንመለከት ፣ እንደሚለፈፈው በአገራችን ውስጥ የሚገኙ ብሄረ-ሰቦች ዕውነተኛ ነፃነትን የተጎናጸፉበት ፖለቲካ ሳይሆን አገዛዙ ለራሱ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲና አገራችንን ለውጭ ኃይሎች ገብቶ መፍተፈቻ መንገድ ያዘጋጀና ለዘለዓለማዊ አለመረጋጋት መንገድ የጠረገ እጅግ አደገኛ የፖለቲካ ስሌት ነው። በዚህ የክልል ፖለቲካ ብሄረ-ሰቦች የባሰውኑ ወደ ጠባብ ስሜትነት እየተገፈተሩ ከሌላው ብሄረ-ሰብ ጋር ተቀላቅለውና ሀሳብ ለሀሳብ ተገናኝተው የመፍጠር ችሎታቸውን በማዳበር ታሪክን እን ዳይሰሩ የታገዱበት በአንግሎ-አሜሪካን የተጠነሰሰ እንደ ኢትዮጵያ የመሰሉ ጥንታዊ ታሪክ ያላቸውን አገሮች እዚያው በዚያው እየተተራመሱ እንዲቆዩ የተደረገበት ልዩ ፖሊሲ ነው። እንደሚታወቀው ይህ አገሮችን በዚህ ዐይነቱ ስትራቴጂ ማመስ የተጀመረው በ70ዎቹ ዐመታት ሲሆን ፣ አሁን ደግሞ እራሳቸውን የማይችሉ መንግስታት/ፌይልድ ስቴትስ/ በሚለው ተንኮለኛ ፖሊሲ እነዚህን መንግስታት የባሰ አዳክሞ ህዝቡ ርስ በርሱ ሲተረማመስ ጥሬ ሀብታቸውን ለመበዝበዝ የታቀደ በምዕራብ መንግስታትና በዓለም አቀፍ ኩባንያዎች የታለመ የረጅም ጌዜ ስሌት ነው። ለእንደዚህ ዐይነቱ ርኩስ የፖለቲካ ስሌት እንደነ ወያኔና በብሄረ-ሰብ ነፃነት ስም የሚንቀሳቀሱ በጠባብ አመለካከት የታወሩ ድርጅቶች ዐይነተኛ መሳሪያ ናቸው።

በአንዳንዶቹ ስሌት ፣ በተለይም ኢህአዴግን በብሄረ-ሰብ ፖለቲካው የሚደግፉት የነፃ አውጪ ታጋይ ነን ባዮች ያልተረዷቸውና የማይረዱቸው መሰረታዊ ጉዳዮች ብዙ ናቸው። በመጀመሪያ ደረጃ ፣ በህብረ-ብሄር ግንባታ ውስጥ የተለያዩ ታሪክ ፣ ባህልና የአኗኗር ስልት ያላቸው የተለያዩ ቤሄረ-ሰቦች አንዱ ከሌላው ጋር ሲቀላቀል ፣ የለመደውን ባህል ይዞ ላይጓዝ ይችላል። ውስጠ-ኃይል ባለውና ቀደም ባለ ታሪክና ተቀማጭነትን ባደበረ ብሄረ-ሰብ ሊዋጥ ይችላል። ሁለተኛ ፣ የተለያዩ ብሄረ-ሰቦች ሲዋሃዱ ለፈጠራና ለስራ የሚያመቻቸውን አዲስ ባህል ያዳብራሉ። ልዩ ቋንቋ በመፍጠር የበለጠ እየተሳሰሩ ማንነታቸውን ይገልጻሉ። ሶስተኛ ፣ በህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ ህብረ-ብሄርን መመስረት ግዴታና ታሪካዊ ነው። በሂደት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ ከፖለቲካ ንቃት ጉድለት የተነሳ ስህተቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ይህንን ግን እንደወንጀል ቆጥሮ ዘለዐለም ማላዘን በሚያንገበግቡ ጥያቄዎች ላይ እንዳናተኩር ያግደናል። አራተኛ ፣ ለአንድ ህብረ-ብሄር የኢኮኖሚ ዕድገት ሰፊ ገበያና በዛ ያለ የሰው ኃይል ያስፈልጋል። በክልል ፖለቲካ ውስጠ-ኃይሉ ከፍተኛ የሆነ የካፒታሊሰት ኢኮኖሚ ለመገንባት አይቻልም። አምስተኛ ፣ የአንድ ህዝብ ባህሉ የበለጠ ሳይንሳዊ መልክ ሊይዝ የሚችለውና የሚዳብረው በአንድ አገር ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች የበለጠ ሲቀራረቡና በአንድ ተቀባይነት ባለው ቋንቋ መግባባት የቻሉ እንደሆን ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ዕድገት በፍጹም ሊኖር አይችልም።

የኢህአዴግን የክልል ፖለቲካን ስንመለከት ከላይ የተጠቀሰውን ታሪካዊ ግዴታ የሚጻረርና የህዝብን የፈጠራ ችላታ እንዲቀጭጭ ያደረገ ፣ እንዲሁም ደግሞ ህዝቡ በፍርሀት ተውጦ አንዱ ሌላውን እየተጠራጠረ እንዲኖር ያደረገ እንጂ በምንም ዐይነት ዕውነተኛ ነፃነትን ያጎናጸፈ አይደለም። ለዚህም ነው ዛሬ በየቦታው ህዝባችን የበለጠ ለረሀብና ለድህነት ታጋልጦ የሚገኘው። ከዚህ ስንነሳ የወያኔ ፖለቲካ ፍልስፍና አልባ ብቻ ሳይሆን ፣ ሆን ብሎ ህዝቡ ተበጣጥሶ እንዲኖራና ውስጣዊ ኃይል አግኝቶ ጠንካራ ኢኮኖሚ እንዳይገነባ ከውጭ ኃይሎች ጋር የተጠነሰሰና ተግባራዊ የሆነ አደገኛ የቦዘኔ ፖለቲካ ነው።

ህዝባዊ ፖለቲካ ግን ከዚህ እቡይ ስሌት የጸዳ ሲሆን ፣ ዐላማውም የአንድን ጎሳ መብት ያላስቀደመ ፣ በትክክለኛ ፍልስፍና ላይ በመመስረት በአንድ አገር ውስጥ የሚኖር ህዝብ በመፈቃቀር በጋራ አገሩን እንዲገነባ የሚጋብዝ ነው። ይህ ዐይነቱ ፖለቲካ በፍልስፍናና በዕወቀት ላይ የተመሰረተ ሲሆን ፣ እያንዳንዱ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚኖር ግለሰብ እርግጠኝነት ተሰምቶትና የዚያ አገር ዜጋ መሆኑን ተረድቶ በአገራዊ ፍቅር በችሎታው ለአገር ግንባታ የሚሳተፍበት ልዩ ብልሀትን ያዘለ የፖለቲካ ፍልስፍና ነው። ለእዚህ ዐይነቱ ፖለቲካ የግንቦት ስምንቱ ምርጫ አንድ ታሪካዊ ምዕራፍ የከፈተ ይመስላል። ከምርጫው ወዲህም የተከሰተው ልዩ ሁኔታ ይህንን በህዝቦች ዘንድ የበለጠ መተሳሰርንና መፈቃቀርን

ያዳበረ ከውስጥ የመነጨ ልዩ ስሜት መሆኑን በየቀኑ ያረጋገጠ ነው። የምርጫውን ውጤት መጭበርበር አስታኮ በተለይም ውጭ አገር በእኛ ኢትዮጵያውያኖች የተካሄደውና የሚካሄደው የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ፣ ውይይትና የሀሳብ መለዋወጥ ዛሬ የሚያረጋግጠው ፣ ኢህአዴግን የሚቃወመው ኃይል በሙሉ በአንድ ዐይነት መንፈስና ስሜት የሚያስተጋባው አገራችን ከእንግዲህ ወዲያ በእንደዚህ ዐይነቱ የተወናበደ ፖለቲካ መራመድ እንደማትችልና ፣ ቂም በቀል ተወግዶና የራስን የግል ጥቅም ወዲያ አሽቀንጥሮ በመጣል ለአንድ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ፣ የእያንዳንዱ ዜጋ መብትና ነፃነት ለሚከበርባት መታግል ነው። የዛሬይቱ ኢትዮጵያ የድሮን የሸኩቻ ታሪክ ለማስተናገድ የማትችል ፣ አንተ አንደዚህ አድርገህ ነበር ፣ በአንተ ምክንያት ነው እንደዚህ ሊሆን የበቃው እየተባባልን የምን ወጃጀልበትን ብልሹ ፖለቲካ ለማየት የማትፈልግ ነች። ዛሬ በውጭም ሆነ በውስጥ ያለው ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆነው ኢትዮጵያዊ ይህንን የትብብር መንፈስና አንድ ላይ ወን ድምና ወንድም ፣ ወንድምና እህት ሆኖ እጅ ለእጅ ተያይዞ ለመጓዝ የተዘጋጀ ነው። በሌላ ወገን ግን እያንዳንዱ ቀደም ብሎ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የተሳተፈ ታሪክን ሳያዛንፍ ራሱም ሆነ ድርጅቱ የፈጸመውን ወንጅልም ሆነ ጥሩ ድርጊት በዝርዝር ቢያቀርብ እንደገና እንደዚህ ዐይነቱ ነገር እንዳይደገም የሚያግዝ መሆኑን ከወዲሁኑ መታወቅ አለበት። ታሪክ ሁልጊዜ መመርመርና መጠናት አለበትና።

## የኛ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ህብረተሰብአዊ ብልጽግናን የሚያመጣ ፣ የወያኔ ድህነትን የሚፈለፍል

ዛሬ በአንዳንዶች የሚነሳ ጥያቄ ፣ በአለፋት አስራ አራት ዐመታት ተግባራዊ የሆነውንና በነፃ ገበያ ስም በአንድ በኩል ጥቂቶችን ያበለጸገ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኛውን የኢትዮጵያ ህዝብ ወደድህነት የገፈተራና አገራችንን የባሰ ጥገኛ እንድትሆን ያደረገ የኢኮኖሚ ፖሊሲ በስተቀር አማራጭ እንደሌለ ነው። እነዚህ ኃይሎች አሁንም ከግሎባላይዜሽንና ከእንደዚህ ዐይነቱ የነፃ ገበያ ፖሊሲ ባሻገር የተለየና በሌሎችም አገሮች ተግባራዊ የሆነ ግለሰብአዊም ሆነ ህብረተሰብአዊ ብልጽግና እንደመጣ ታሪክን ለማገላበጥና ለማወዳደር በፍጹም ለማመን አይፈልጉም። ከዚህም በመነሳት ዐይናቸውን ጭፍን አድርገው ፣ ጆሮአቸውን ዘግተው የዛሬውን ሁኔታ ሌላም ኃይል ቢመጣ ከዚህ የተለየ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለማካሄድ እን ደማይችልና ሊለውጠውም እንደማይችል ይምላሉ ፤ ይገዘታሉ። ይህ የፖለቲካ ኢኮኖሚክስን ህግና ታሪክን ካለማወቅ የሚመነጭ ጭፍን ያለ ክርክር አንዳንዶችን ምናልባት ሊያደናብር ይችላል። ለኛ ኢትዮጵያውያን ዲሞክራቶች ግን የኢትዮጵያ ህዝቦች ዕድልና ዕጣ እንዲሁም ታሪክን መስራት ከዛሬው ድህነትን ከፈለፈና አገራችንን ካዋረደ ፖሊሲ ባሻገር መታየት እን ዳለበት እንደ ጠራ ውሀ ግልጽ ሆኖ የተቀመጠ አቋማችን ነው።

ለመሆኑ በአለፋት አስራ አራት ዐመታት ውስጥ ምን ዐይነት የኢኮኖሚ ፖለቲካ ነው የተካሄደው ? የነፃ ገበያ ፖሊሲስ የግዴታ ይህንን መመሰል አለበት ወይ ? ብለን መጠየቅና መልስ መስጠት አለብን። ይህ ፀሀፊና ሌሎችም ለአገር በመቆርቆር የሚታገሉ ኢትዮጵያውያን አዳማጭ ካገኙ የአቅማቸውን ያህል የኢህአዴግን የነፃ ገበያ ፍልስፍናና መዘዙን አሳይተዋል። በተጨማሪም ደግሞ ራሱ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ እን ደሚያረጋግጥው ብዙ ትንተናና ጥያቄ የማያስፈልገው ድህነት ከምን ጊዜውም በበለጠ ሁኔታ ዐይኑን አፍጦ አግጦ ይታያል። ይህ ለኛ ከኢትዮጵያ ህዝቦች ጎን ተሰልፈን ለምንታገለው ግልጽ ቢሆንም የኢህአዴጉ የገበያ ኢኮኖሚ ፍልስፍና ለምን ህብረተሰብአዊ ብልጽግናን ለማምጣት እንደማይችል ደግሞ ደጋግሞ ማመልከት ታሪካዊ ግዴታችን ነው።

ኢህአዴግ የእነ አይ ኤም ኤፍን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሲከተል ከመጀመሪያወኑ ግልጽ የሆኑና በብዙ አገሮች ተሞክረው ህዝባዊ ጠቀሜታን ያላመጡና እርስ በርሱ የተሳሰረ ኢኮኖሚ እን ዳይዳበር በር ያልከፈቱ ፖሊሲዎች እንደማረጋገጫ ሊከተላቸው በፍጹም አልፈለገም። እ.አ. አቆጣጠር ከሰማንኛው ዓ.ም ጀምሮ በጋና ፣ በዚምባቤና በአይቮሪ ኮስትና በሌሎችም የአፍሪቃ

አገሮች የተካሄዱት የመዋቅር ማስተካከያ ፖሊሲዎች እነዚህን አገሮች የባሰ የዕዳ ወጥመድ ውስጥ እንደከተታቸውና ኢኮኖሚያቸውም የበለጠ ወደ ውጭ እንዲያተኩርና በአንድ ወይም በሁለት ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ የእርሻም ሆነ የጥሬ ሀብት ውጤቶች ላይ ብቻ እንዲመኩና ይህም መቀመቅ ውስጥ እንደከተታቸው እንደተመክሮ ሊቀርቡ የሚችሉ መሰረተ ሀሳቦች ነበሩ። ይህንን ለመገንዘብ ያልፈለገው የወያኔ አገዛዝ በእክክልኝ ልክክልህ ኢኮኖሚ ፖሊሲው በማንአልኝበት ህግና ስርዓትን በመጣስ የአገሪቱን ሀብት በመጠቅለልና አንዳንድ ከበርቴዎችን ደግሞ ከውጭ በማስገባት ኢኮኖሚውን ማዛባት ተያያዘው። ይህ በነፃ ገበያ ስም ሲለፈፍ የነበረው ፖሊሲ የአገሪቱን ገበያ ለውጭ ምርት ክፍት በማድረጉ ወደ ውስጥ የምርት ክንውንን በማዳካም ብዙ ሰራተኛ ከስራው ቦታ እንዲፈናቀልና ወደድህነት ዓለም እን ዲዛወር አደረገ። የነፃ ገበያው ፖሊሲ በመሰረቱ ሳይንስና ቴክኖሎጂን ማስቀደምና የአገር ውስጥ ከበርቴዎችን ማዳበር ሲገባው አብዛኛውን እንደ ሃምሳዎቹ ዓመታት ወደ አገልግለት መስክ እንዲሰማሩ በማድረግ በአገር ውስጥ በሚመረት ምርትና ከውጭ በሚመጣ ሸቀጣ ሸቀጥ መሀከል ከፍተኛ መዛባት እንዲፈጠር አደረገ። የኢኮኖሚው ፖሊሲ በየኢኮኖሚ መስኮች መሀከል ውስጣዊ ግኑኝነት እንዲመሰረትና ጠቅላላው የኢኮኖሚው አወቃቀር ውስጣዊ-ኃይል እንዲያገኝ ሆኖ ሊደራጅ ባለመቻሉ በአገሪቱ ውስጥ በየክልሎች መሀከል የዕድገት መዛባትና የሀብት መባከን እንዲፈጠር አድርጓል። በተጨማሪም ወደ ኢኮኖሚው ውስጥ የሚፈሰው ገንዘብ ከምርት ክንውን ጋር በቀጥታ ለመያያዝ ባለመቻሉ የዋጋ ሽቅበትን በማስከተል ወደውስጥ የሚመረተው ጥቂት ምርትም ሆነ ከውጭ የሚመጣውን ገዝቶ ለመጠቀም የሚችለው የህብረተሰብ ክፍል በጣም ጥቂቱ ብቻ ሆነ። የአገሪቱን ገበያ ለውጭ ዕቃ ክፍት ማድረጉ ለመዋዕለ-ነዋይ የሚሆነውን የውጭ ገንዘብ ከማባከኑም በላይ ሳይሰራ ፍጆታን የሚጠቀም አዲስ የህብረተሰብ ክፍል ብቅ እንዲል አድርጎ የባህል ውድቀትን አስከተሏል። በዚህ የአገር ውስጥን የምርት ክንዋኔን ያዳከመና ከፖለቲካ ኢኮኖሚ ህግ ጋር የማይጣጣም ፖሊሲ የውጭ ንግድ ሚዛኑን ማዛባቱ ብቻ ሳይሆን አገራችንን የባሰ በዕዳ እን ድትተበተብና መንግስትም ራሱም ለባጀት መሚያው በውጭ ድጎማ ጥገኛ እንዲሆን ተገደደ። በአሁኑ ወቅት አርባ በመቶ የሚሆነው የአገሪቱ ባጀት በውጭ የሚደጎም ለመሆኑ የተረጋገጠ ነው። ይህም የሚያመለክተው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአለፉት አስራ አራት ዓመታት ከምርት ክንውን ይልቅ ወደ አገልግሎት መስኩ እያደለ እንደመጣ ነው። ለምሳሌ የየሴክተሮችን በጠቅላላው የምርት ክንውን(ጂዲፒ) ዕድገት ላይ ያላቸውን አስተዋጽኦ ስንመለከት ፣ የኢን ዱስትሪው መልክ አስር በመቶ ብቻ ድርሻ ሲኖረው ፣ የእርሻው መስክ አርባ አምስት በመቶ ፣ የአገልግሎት መስኩ ደግሞ አርባ አራት በመቶ ድርሻ አላቸው ማለት ነው። ይህም የሚያረጋግጠው አሁንም ቢሆን የኢንዱስትሪ መስኩን ለማሳደግና የጠቅላላው ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ለማድረግ የተወሰደ ፍቱን እርምጃ እንደሌለ ነው። ከዚህ ባሻገር የአትዮጵያ ኢኮኖሚ እ.አ ከ1994/95 ጀምሮ እስከ 2000/01 በአማካይ በ4.8 በመቶ አደገ ቢባልም ድህነት እየተስፋፋና የህዝቡም ዐመታዊ ገቢ እየቀነሰ እንደመጣ ስታትስቲክስ ያሳያል።

ከዚህ ስንነሳ የኢህአዴግ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ በመሰረቱ ነፃ ገበያ ሳይሆን ካፒታሊዝም በሳይንስና በቴክኖሎጂ እየተደገፈ እንዳይዳብርና እንዳይስፋፋ ፣ እንዲሁም የአገር ውስጥ ከበርቴ ብቅ እንዳይል ያገደና ገንዘብ ያለውንም ሀብቱን ባልባሌ ቦታ ላይ እንዲያባክን መን ገደድ የከፈተና የገፋፋ ነው። በእዚህ ዐይነት የኢኮኖሚ ፖሊሲ አገራችን ከምንግዜውም የበለጠ መቀመቅ እየገባችና ሁኔታውም ውስብስብ እየሆነ በመምጣት ላይ ነው። የአለውም አማራጭ ከዚህ ዐይነቱ የተበላሸ የገበያ ኢኮኖሚ ፍልስፍና መላቀቁ የማያወላዳ መንገድ ነው።

የኛ ከሰፊው ህዝብ ጎን ቆመን የምንታገል ኃይሎች አቋም የገበያን ኢኮኖሚ ጤናማ በሆነ መንገድ ማሳደግ ይሆናል። ለዚህ መሰረቱ ደግሞ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተደገፈ ጠቅላላውን ህዝብ የሚጠቅም ፣ ቀስ ቀስ እያለ በእርግጥ ደግሞ እያደገና እየተስፋፋ ለውስጥ ውድድር በር የሚከፍት የኢኮኖሚ ፖሊሲ መከተል ይሆናል። ወደ ውስጥ ኢኮኖሚውን ለማደራጀትና ጠቅላለው ህዝብ በኢኮኖሚ ግንባታ ላይ እንዲሰማራ ኢኮኖሚው በሶስት መልኮች ግልጽ በሆነ ሁኔታ መቀመጥ አለበት። በመጀመሪያ የመንግስት ሚና

በኢኮኖሚው ውስጥ በግልጽ ይሰፍራል። በሁለተኛ ደረጃ የአገር ውስጥ ከበርቴ ከንግድ መስክና ካልባሌ የአገልግሎት መስክ እየተላቀቀ ወደ ምርት ክንውን እንዲያዘነብል ማን ኛውንም የምክርና የሞራል እንዲሁም ቴክኒካዊ ርዳታዎችና አጠቃላይ የአደረጃጀትና የገበያ አጠቃቀም ትምህርት ስልት ይሰጣል። በሶስተኛ ደረጃ በህብረት ለመንቀሳቀስ ለሚፈልጉ ግለሰቦች አስፈላጊው የማቴሪያልና በዝቅተኛ ወለድ ላይ የተመሰረተ ብድር ይሰጣል። ከዚህ ባሻገር የባንኩ መስክ አገሪቱን ሊጠቅም በሚችል መስክ በማደራጀት ፣ የገንዘብ እንቅስቃሴ ክምርት ክንውን ፣ ከሳይንስና ከቴክኖሎጂ ዕድገት ጋር እንዲያያዝ ይደረጋል። ልዩ ኢን ቬስትሜንት ባንክ በማቋቋም በህዝብ ውስጥ የሚንቀሳቀሰውንና ቤት ውስጥ የተኛው ገንዘብ በመንግሰት ቦንድ አቅራቢነት ለምርት ክንውን እንዲውል ይደረጋል። በሌላ አነጋገር ፣ በፌዴራል ፣ በክፍለ አገርና በየወረዳዎች ለአገር ግንባታ የሚያገለግል የመንግስት ልዩ ሰርተፊኬት በማተም ህዝቡ ገንዘቡን በወለድ እንዲያስቀምጥ ልዩ የገንዘብ ገበያ በባንኮች አማካይነት እንዲዘጋጅ ይደረጋል። በዚህ መስረት ብቻም በህዝብ ውስጥ ያለውን የተኛ ገን ዘብ ማንቀሳቀስና ከምርት ክንውን ጋር ማያያዝ ይቻላል።

በእርሻው መስክ የመንግስት ሚና ገበሬው ቀጥተኛ የመሬቱና የምርቱ ባለቤት እንዲሆን የሚያደርግ ሲሆን ገበሬው በተለያዩ ለምግብና ለጥሬ ሀብት ሊያገልግሉና በፋብሪካ አገር ውስጥ ሊፈበረኩ በሚችሉ ምርቶች ላይ እንዲሰማራ ምክርና ልዩ ልዩ ርዳታዎች ያቀርባል። ገበሬው የራሱን ሀብት ሊያንቀሳቅስ የሚችልበትና በቀላሉ ብድር ሊያገኝ የሚችልበት የህብረት ባንክ እንዲቋቋም ይደረጋል። የተወሰነው ገበሬ ለማገዶ ፣ ለቤት ስራና ለአካባቢ እን ክብካቤ ሊያገለግሉ በሚችሉ የዛፍ ተከላዎች ላይ እንዲሰማራና በኢኮኖሚም ቀጥተኛ ተጠቃሚ እንዲሆን አስፈላጊው ምክርና ርዳታ እንዲሰጥ ይደረጋል። በተጨማሪም ገበሬው የኬሚካል ማደበሪያና "የምርጥ" ዘር ጥገኛ እንዳይሆን አስፈላጊው ምክርና አማራጭ ኦርጋኒክ ማደበሪያ ይቀርብለታል። ገበሬው እስካሁን ከተተበተበበት ዕዳ እንዲላቀቅ መንግስት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል። ገበሬው ራሱ የመጨረሻው ውጤት ተጠቃሚ ብቻ ሳይሆን ዘመናዊ የምርት አመራረትን ሁኔታ እንዲያጠናና ተግባራዊ እንዲያደርግ በገጠር ውስጥ የዕደ-ጥበብ ሙያ እንዲስፋፋ በማድረግ በእርሻ ምርትና በዕደ-ጥበብ ሙያ መሀከል የጠበቀ ግኑኝነት እንዲመሰረት አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል። ከዚህ በተረፈ ገበሬው ከውጭ በሚመጣ ምርት እንዳይመታ የገበሬውን የእርሻ ውጤት የሚቀናቀኑ የውጭ ምርቶች ሁሉ አይ ሙሉ በሙሉ ይታገዳሉ። ካለበለዚያ በከፍተኛ ቀረጥ እንዲገደቡ ይደረጋል።

ከዚህ ባሻገር መንግስት ከተማዎችን ለመገንባት የሚያስችልና ፣ አገሪቱ ባህል የሚዳብርባት አገር እንድትሆን አስፈላጊውን የሀብት ማንቀሳቀሺያና የገንዘብ ስብሰባ መንገድ በመተለም ለመገናኛና ለመንገድ ስራ በማዋል አገራችን በአንድ ትውልድ አሁን ካለችበት ሁኔታ ተላቃ በአስተማማኝ ተቋም ላይ እንደተገነባና ለሚቀጥለው ትውልድ እንደትሸጋገር አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል። ለዚህ የሚያገለግል ልዩ በአገር ውስጥና በውጭ አገር በሚገኙ ኢትዮጵያውያን የሚሰበሰብ ልዩ የገንዘብ ፈንድ ይዘጋጃል። ይህ ገንዘብ ከመንግስትና ከግለሰብ ሀብታሞች ጋር ተደምሮ ለባቡር ሀዲድ መስሪያና ለሌሎች ትላልቅ ፕሮጀክቶች እን ዲውል ይደረጋል። በዚህ ሰፊ የአገር ግንባታ ሂደት ውስጥ ወጣቱ ልዩ አትኩሮ ተሰጥቶት በልዩ ልዩ ሙያዎች እንዲሰለጥን ይደረጋል።

ይህ ዐይነቱ በቅድሚያ የአገርን ሀብት ማንቀሳቀሺያና ለኢኮኖሚው ዕድገት መገልገያ እን ዲሆን ማድረግ በቀጥታ የህዝቡን የማተሪያል ሁኔታ ለማሻሻል እንጂ የገበያ ኢኮኖሚን እንደ ዐላማ አድርጎ የሚወሰድ የኢኮኖሚ ፍልስፍና አይደለም። በሌላ አነጋገር በካፒታሊስት ኢኮኖሚ ሎጂክ ላይ የሚንቀሳቀስው ኢኮኖሚ ጠቅላላውን ህዝብ የሚጠቅም ፣ የሀብት ክፍፍል እንዳይዛባ የሚያደርግና በህብርተሰብ ውስጥ ህብረተሰብአዊ ቅራኔ እንዳይፈጠር የሚያደርግ የኢኮኖሚ ፖሊሲ መሆን አለበት። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ መንግዱ ከተዘጋጀለት ሊሰራና እራሱን ጠቅሞ ህብረተሰቡን ሊጠቅም እንደሚችል በግለሰብ ሀብት ማዳበርና ህብረተሰቡ የኢኮኖሚው ዕድገት ተጠቃሚ እንዲሆን የመንገስትም ሆነ ልዩ ልዩ መንግስትና መንግስት ነክ ያልሆኑ ኢንስቲቱሽኖች ታሪካዊና የሞራል ሀላፊነት ይሆናል። ደሀና ሀብታም

ተፋጠው በሚኖሩበት አገር ፣ ጥቂቱ ሀብታም እየሆነ ፣ አብዛኛው ደግሞ ወደድህነት የሚገፈተር ከሆነ ሀብረተሰብአዊ መረጋጋት ይኖራል ብሎ ማሰብ በፍጹም አይቻልም።

ይህንን ዐይነቱን አገርን በፀና መሰረት ላይ እንዲገነባ የሚያደርግ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ወያኔም ሆነ የውጭ ኃይሎች አጥብቀው ይጠላሉ። የነሱ ዐላማ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች ፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ባለቤት እንዳይሆኑ ማድረግ ፣ ቀንጆ ቀንጆ ከተማዎችን እንዳይገነቡ እንቅፋት መሆን ፣ ሀብት በጥቂት ሰዎች እጅ ተከማችቶ ወደ ውጭ እንዲፈስ ማድርግ ነው። በአገራችን ምድር የላቲን አሜሪካ ሁኔታ ተፈጥሮ የውጭ ከበርቴዎችና የውስጥ ፀረ-ዲሞክራሲው አገዛዝ በእከክልኝ ልከክልህ ፖለቲካቸው የአገሪቱን ሀብት የሚዘርፉበትና ወደ ውጭ በማፍሰስ ድህነትንና ነፍሰ ገዳይን  የሚፈለፍሉበትና ሁኔታ ለመፍጠር ነው። ከአስራ አራት ዐመት ጀምሮ በዓለም ባንክ ፣ በአይ ኤም ኤፍና በአሜሪካኑ በሰለላ ድርጅት የተተበተበው የተራድኦ ድርጅት ተብዬው የተመሰረተው የስራ ክፍፍል ይህንን ሁኔታ ለመፍጠር ነው። በአጭሩ ህዝቡ የተዝረከረከ ኑሮ እንዲኖርና አገራችንም የዓለም አቀፍ ኮሙኒቲን ቡራኬ እያገኘች እንደትኖር የሚያደርግና ለውርደት የሚጥል የገበያ ኢኮኖሚ ነው። የዛሬው ትግላችንም ከዚህ የተበላሸ የገበያ ኢኮኖሚ ፍልስፍና ተላቆ ህዝባችን የሚመኘውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ በላይኛው መልክ መንደፍ ይሆናል። ትግሉ ውስብስብ ቢመስልም ለአንድ ዐላማ በአንድ መንፈስ ከተነሳን በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚ የማንገነባበት ምንም ምክንያት የለም።

ዲሞክራሲና ነፃነት ለኢትዮጵያ ህዝብ !!

ፈቃዱ በቀለ ከበርሊን

<u>ማሳሳቢያ ፣</u>

ይህ ጸሀፊ የማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል አይደለም። ይሁንና ቅንጅትም ሆነ በውጭ የሚገኘው የህብረት አመራር አገራችን ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲሰፍን የሚያደርጉት ትግል በአሁኑ ወቅት አማራጭ የሌለው እንቅስቃሴ ነው ብሎ ያምናል። በተለይም የቅንጅት መመስረትና በምርጫ ውስጥ መሳተፍ ታሪካዊ እንደሆነና ፣ ቅንጅት ባይመሰረት ኑሮ እኛን የተበታተነን ኃይሎች ሊያሰባስብ የሚችል ሰፊ የፖለቲካ መድረክ ሊፈጠር እንደማይችል ይህ ጸሀፊ በቅን መንፈስ መዝግቧል። ቅንጅት ይዞ የተነሳው መን ፈስና የትግል ዐርማ የሁላችንም ስለሆነ አባል ሆን አልሆን ትግሉ የሁላችንም መሆኑን ተገን ዝበን ለዲሞክራሲትና ለነፃ ኢትዮጵያ የምናደርገውን ትግል መቀጠል ይኖርብናል ብዬ አምናለሁ። በፖለቲካ ሂደት ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ስህተቶች በመደማመጥና በውውይት ሊፈቱ የሚችሉ ስለሆነ ፣ የአመራር ችግሮች ቢፈጠሩ እነሱን ማጋነን ትግሉን ሊያዳክመው ይችላል። በዚህ መንፈስ ከሰራንና ለሚሆንና ለማይሆን አሉባልታ በር ካልከፈትን ለዲሞክራሲ ትግሉ ትልቅ አስተዋፅኦ እንደምናበረክትና የአገራችንን ብሄራዊ ነፃነትና አንድነት የሚቀናቀኑትን ኃይሎች በጋራ ታግለን እንደምናሸንፍ ጽኑ ዕምነት አለኝ።